**ፖሊሲ፦ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ**
**ብቁ ያለመሆን የይግባኝ ፖሊሲ እና ሂደት**
**የበጀት አመት 2022 (FY22)**
**ኦገስት 25፣ 2022**

**የዘመነው፡ ሴፕቴምበር 15፣ 2022**

**የዚህ ፖሊሲ ዳራ፣ስልጣን እና አላማ**
የኤርሊ ቻይልድሁድ ፍትሃዊ ካሳ ቡድን ጊዜያዊ የማሻሻያ ህግ ለኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች በኤርሊ ቻይልድሁድ ፍትሃዊ ካሳ ቡድን ምክሮች ስምምነት አቻ ክፍያ ለመደገፍ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ለመክፈል ለኦፊስ ኦፍ ዚ ስቴት ሱፐርኢንተንደንት ኦፍ ኤጁኬሽን ስልጣን ሰጥቷል። በFY22፣ OSSE የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያን ለማስተዳደር፣ በደረጃው ቀልጣፋ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ቀጥተኛ የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞችን ለማስተዳደር ከተዘጋጀ ማህበራዊ ተጽዕኖ ከሚያደርግ ኩባንያ፣ AidKit ጋር እየሰራ ነው። የገንዘብ ድጋፍ ለመቀበል፣ ብቁ የሆነ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች በ AidKit የመሳሪያ ስርዐት ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው።

የOSSE፣ ግብ እና አላማ ሁሉም የብቁነት መስፈርቶችን የሚያሟሉ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች በኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ በኩል ተጨማሪ ክፍያ እንዲቀበሉ ነው። በዚያ ምክኒያት፣ OSSE እና AidKit የህዝብ የገንዘብ ድጋፎችን ታማኝነት ለመጠበቅ እና ብቁ ላልሆኑ ግለሰቦች ስርጭትን ለመከላከል ብቁ የሆኑ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች በዝቅተኛ ገደብ ለገንዘብ ድጋፎች ብቁነታቸው እንዲያረጋግጡ ለማድረግ የሚፈልግ ሂደት ነድፈዋል።

ለዚህ ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ ብቁ ሊሆኑ የሚችሉት ብዙ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች በመሆናቸው ምክኒያት በእውነት ብቁ ለሆኑ ለአንዳንድ ግለሰቦች ብቁነትን ማረጋገጥ ላይቻል ይችላል። ብቁ የሆነ አመልካች ብቁ ሳይሆን ሊገኝ የሚችልበት ሊሆኑ የሚችሉ ምክኒያቶች ሊያካትቱ የሚችሉት፦ በቅድመ ትምህርት ፈቃድ ሰጪ መሳሪያ (DELLT) ክፍል ውስጥ በሰራተኛው ሰው ቀጣሪ የገባ የተሳሳተ መረጃ፣ አመልካች ማመልከቻውን ሲያስገባ በፈጸማቸው ስህተቶች፣ ልዩ የግል ሁኔታዎች ወይም ሌሎች ምክኒያቶች።

አንድ አመልካች ለገንዘብ ድጋፎች በስህተት ብቁ እንዳልሆነ መወሰኑን ካመነ፣ አመልካቹ ውሳኔውን ለOSSE የቅድመ ትምህርት ክፍል ይግባኝ ሊጠየቅ ይችላል

**ለይግባኝ ተቀባይነት ያላቸው ምክኒያቶች**
OSSE በሚከተሉት ምክኒያቶች ለገንዘብ ድጋፎች ብቁ እንዳልሆኑ የተወሰነባቸውን አመልካቾች ይግባኝ ግምት ውስጥ ያስገባል፦

- የአመልካች ስራ በDELLT መረጋገጥ አይችልም፣ ወይም
- በDELLT ውስጥ የአመልካች የመጀመሪያ ወይም የተለዩበት ቀናት የብቁነት መስፈርትን አያሟላም፣ ወይም
- አመልካቹ በ DELLT ውስጥ ለተጨማሪ ክፍያ ብቁ ባልሆነ "የሰራተኛ አይነት" ተመድቧል፣ ወይም
- ከላይ ካሉት መስፈርቶች ማንኛውም ጥምረት።

ከላይ ላሉት ለማናቸውም ምክኒያቶች ብቁ ያለመሆን ውሳኔን ይግባኝ ለመጠየቅ፣ አንድ አመልካች በ OSSE ፈቃድ ባገኘ የህጻን እድገት ፋሲሊቲ ውስጥ እንደሚሰሩ የሚያብራራ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፤ የስራ ቀናት እና/ወይም መደበኛ የስራ ሃላፊነቶች ተቀባይነት ላለው ማስረጃ ምሳሌዎች ተጨማሪ መግለጫ ሀ ይመልከቱ።

**ለይግባኝ ተቀባይነት የሌላቸው ምክኒያቶች**
OSSE በ AidKit የመሳሪያ ስርዐት ውስጥ ሙሉ ማመልከቻቸውን ለሞሉ እና ላስገቡ አመልካቾች ብቻ ይግባኞችን ይመለከታል። ሙሉ ማመልከቻውን ያልሞሉ እና ያላስገቡ ግለሰቦች ይግባኝ ማቅረብ አይችሉም።

OSSE ለተጨማሪ ክፍያ ብቁ ሆነው ለተገኙ ነገር ግን የክፍያ መጠናቸው በሚመሰረትበት "የሰራተኛ አይነት" የማይስማሙ አመልካቾችን የክፍያ መጠን ይግባኞች አይመለከትም። ለክፍያ ብቁ ሆነው ለተገኙ አመልካቾች፣ በ DELLT ውስጥ የተዘረዘረው "የሰራተኛ አይነት" የክፍያ መጠን የመጨረሻ ወሳኝ ነው።

**(ሴፕቴምበር 15፣ 2022 የዘመነ)** OSSE ብቁ ባልሆኑ ፋሲሊቲዎች ውስጥ የተቀጠሩ አመልካቾችን ይግባኝ አይቀበልም (ለምሳሌ፣ በ የዲ.ሲ. የመንግስት ትምህርት ቤቶች (ዲ.ሲ. ፓብሊክ ስኩልስ) የተቀጠሩ ኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች)፣ በ OSSE ፍቃድ ያልተሰጠው የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ወይም ምንም አይነት ፋሲሊቲ)።

**ለተፈቀዱ ይግባኞች መስፈርቶች**

*ፈቃድ ባለው የህጻን እድገት ድርጅት ውስጥ ከመቀጠር ወይም ከስራ ቀናት ጋር የተያያዙ የብቁነት ይግባኞች*

OSSE አንድ አመልካች በሜይ 16፣ 2022 እና ግለሰቡ ይግባኝ በጠየቀበት ቀን መካከል በ OSSE ፈቃድ ባለው የህጻን እድገት ፋሲሊቲ ወይም ድርጅቶች ውስጥ የግለሰቡን ቀጣይነት ያለው ስራ የሚያረጋግጥ መረጃ (ለምሳሌ፣ የክፍያ መግለጫዎች፣ መደበኛ የውል ደብዳቤ ወይም የጀመሩበትን ቀን የሚያሳይ የቅጥር ውል) ማቅረብ ከቻለ ይግባኙን ይመለከታል። ከአንድ ወር ያነሰ የስራ ክፍተት ለFY22 የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ይግባኝ አላማዎች ቀጣይነት ላለው ስራ እንደ ክፍተት አይቆጠርም። በስራ ቀናት መሰረት የብቁነት ይግባኝ ያቀረቡ ግለሰቦች ይግባኙ ሙሉ በሙሉ እስኪታይ ድረስ አሁን ባሉበት ቦታ ተቀጥረው መቆየት አለባቸው።

*ከ "ሰራተኛ አይነት" ጋር የተያያዙ የብቁነት ይግባኞች*

OSSE የአመልካቹ የ "ሰራተኛ ዓይነት" እንደ "ሌላ፣" "ምትክ፣" ወይም "የቤት ረዳት/ምትክ" ከተዘረዘረ ይግባኙን ከግምት ውስጥ ሊያስገባው ይችላል እናም አመልካቹ የመጀመሪያ የስራ ሃላፊነቶቹ የመጀመሪያ እንክብካቤ እና የትምህርት አገልግሎቶችን ለልጆች ማቅረብ ላይ እንደሚያተኩር፣ እንዲሁም ቢያንስ 10 ሰዓት በሳምንት ወይም ከስራ ሰዓታቸው ቢያንስ 60 ፐርሰንት የሚሆነውን (ከሁለቱ የሚበልጠውን) የልጆች ዕድገት ቤት ወይም የልጆች ዕድገት ማዕከል ክፍሎች ውስጥ ለልጆቹ የመጀመሪያ እንክብካቤ እና ትምህርት አገልግሎቶችን እየሰጡ እንደሚያሳልፉ ማሳየት ይችላል። የስራ ሃላፊነቶችን ተቀባይነት ያለውን ማስረጃ ለማግኘት አባሪ A ን ይመልከቱ።

OSSE በ DELLT ውስጥ የአመልካቹ የ "ሰራተኛ ዓይነት" "ዳይሬክተር" ከሆነ አመልካቹ የሙሉ ጊዜ የክፍል አስተማሪ ሆኖ እንደ ረዳት ዳይሬክተር የሚያገለግል ከሆነ እና የረዳት ዳይሬክተሩ ተቀዳሚ ሃላፊነት እንደ የክፍል አስተማሪ እንደሆነ እና አብዛኛውን የስራ ሰዓታቸውን በክፍል ውስጥ የማስተማር ሃላፊነታቸውን እየተወጡ እደሚያሳልፉ የሚያረጋግጥ የፅሁፍ መግለጫ ከፋሲሊቲው ዳይሬክተር የሚያቀርቡ ከሆነ ብቻ ይግባኙን ከግምት ውስጥ ያስገባል። OSSE በ DELLT ውስጥ ያለው የ "ሰራተኛ ዓይነት" "ዳይሬክተር" ከሆነ አመልካቾች የሚመጡ ማመልከቻዎችን ከግምት ውስጥ አያስገባም።

**የይግባኞች ሂደት**

ብቁ ሆነው ያልተገኙ አመልካቾች ብቁ አለመሆናቸውን የሚያሳውቅ እና አመልካቹ ብቁ ሆነው ያልተገኙበትን ምክንያቶች የሚያካትት ተግባቦት ከ AidKit ይቀበላሉ። ተግባቦቱ የ AidKit መድረክ ግላዊ ማስፈንጠሪያን ጨምሮ አመልካቹ ይግባኝ እንዴት እንደሚያስገባ የሚያሳይ መመሪያ ያቀርባል። ይግባኝ ማለት የሚፈልጉ ውድቅ የተደረጉ አመልካቾች የብቁነት ውሳኔው ስህተት እንደሆነ ለምን እንደሚያምኑ የሚያሳዩ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማቅረብ እንዲሁም አጋዥ ሰነዶችን (ለምሳሌ የስራ ቅጥር ማስረጃ፣ የስራ ቅጥር ወይም የስራ ሃላፊነቶች ቀን፤ በአባሪው ውስጥ ተቀባይነት ያገኙ ሰነዶችን ይመልከቱ) በ AidKit መድረክ በኩል ለመጫን ግላዊ ሊንኩን ሊጠቀሙ ይችላሉ። አመልካቾች ከ AidKit ማሳወቂያ ከተቀበሉ በኋላ ባሉት 10 የስራ ቀናት ውስጥ በ AidKit መድረክ በኩል የእነርሱን ይግባኝ እና አጋዥ ሰነዶች ማስገባት አለባቸው። ከ AidKit ማሳወቂያ ከ 10 የስራ ቀናት በኋላ የገቡ ማመልከቻዎች ከግምት ውስጥ አይገቡም።

<u>ሰነዶች እና ሌሎች የግል መረጃዎች በኢሜይል መላክ የለባቸውም።</u>

የ OSSE የ DEL ሰራተኞች አመልካቹ ይግባኝ እና አጋዥ ሰነዶችን ካስገቡ በኋላ ባሉት **30** የስራ ቀናት ሁሉንም የይግባኝ ጥያቄዎች ይገመግማሉ እንዲሁም የቀረበው ማስረጃ፣ በ [የቀዳሚ ልጅነት ጊዜ አስተማሪ ክፍያ ዋጋ ፈንድ ፖሊሲ የልጅ እንክብካቤ ሰራተኞች ብቁነት እና የክፍያ መጠኖች (Child Care Staff Eligibility and Payment Amounts for Early Childhood Educator Pay Equity Fund policy)](#) ላይ በዝርዝር እንደተቀመጠው፣ ለተጨማሪ ክፍያ አመልካቹ የብቁነት መስፈርቶቹን ማሟላቱን ማሳየት አለማሳየቱን ይወስናል። በዚህ ወቅት፣ የ DEL ሰራተኞች በይግባኙ የቀረበውን መረጃ ለማጣራት አመልካቹን ወይም የአመልካቹን አሰሪ ሊያነጋግሩ ይችላሉ። የ DEL ውሳኔን የሚገልጽ የጽሁፍ መልዕክት ለይግባኝ ባዩ የሚላክ ይሆናል። ውሳኔው የመጨረሻ ነው።

አመልካቹ በይግባኛቸው ምክንያት ለተጨማሪ ክፍያ ብቁ ሆነው ከተገኙ፣ አመልካቹ የማመልከቻቸውን ቅቡልነት እንዲሁም ተጨማሪ ክፍያቸውን ለመቀበል መቼ መጠበቅ እንደሚችሉ የሚያሳውቅ ተጨማሪ ተግባቦት ከ AidKit ይቀበላሉ። በይግባኝ ብቁ ሆነው የተገኙ

አመልካቾች በመጀመሪያ ማመልከቻቸው ውስጥ የቀረበውን መረጃ መሰረት በማድረግ ክፍያ ይቀበላሉ እንዲሁም ለ AidKit አዲስ ማመልከቻ ማስገባት አያስፈልጋልቸውም።

OSSE አመልካቹ በ DELLT ውሂብ ውስጥ ባሉ ስህተቶች መሰረት በመጀመሪያ ብቁ እንዳልሆነ የተወሰነበት እንደነበረ ከወሰነ፣ OSSE የ DELLT ውሂቡ መዘመኑን ለማረጋገጥ አመልካቹ ከተቀጠረበት ፋሲሊቲ ጋር ይሰራል።

**ጥያቄዎች**
ይህን ፖሊሲ የተመለከቱ ጥያቄዎች በ OSSE.DELCommunications@dc.gov መላክ ይችላሉ።

**አባሪ፦ የስራ ቅጥር እና የስራ ሃላፊነቶች ተቀባይነት ያለው ማስረጃ**
*የስራ ቅጥር ተቀባይነት ያለው ማስረጃ እና የስራ ቅጥር ቀን*

- በተቀመጠው ቀን ቅጥርን የሚገልጹ የክፍያ መግለጫዎች ወይም የክፍያ ደረሰኞች
- የግለሰቡን ስም፣ የአሰሪ ስም፣ የጀመረበት ቀን፣ የስራ ሰዓት እና የስራ ሃላፊነቶችን የሚዘረዝር እና በአሰሪው እና በተቀጣሪው የተፈረመ መደበኛ የቅጥር ደብዳቤ ወይም የስራ ቅጥር ውል

*የስራ ሃላፊነቶች ተቀባይነት ያለው ማስረጃ*
አመልካቹ ቢያንስ 10 ሰዓት በሳምንት ወይም ከስራ ሰዓታቸው ቢያንስ 60 ፐርሰንት የሚሆነውን (ከሁለቱ የሚበልጠውን) የልጆች ዕድገት ቤት ወይም የልጆች ዕድገት ማዕከል ክፍሎች ውስጥ ለልጆቹ የመጀመሪያ እንክብካቤ እና ትምህርት አገልግሎቶችን እየሰጡ እንደሚያሳልፉ ለማሳየት፣ አመልካቹ ከሚከተሉት የሰነድ ዓይነቶች ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ማቅረብ አለበት፦

- የግለሰቡን ስም፣ የስራ ሰዓት፣ እና የስራ ሃላፊነቶች የሚዘረዝር መደበኛ የቅጥር ደብዳቤ፣ የስራ ቅጥር ውል ወይም የስራ መግለጫ
- የስራ ሃላፊነቶቻቸውን እና ዓይነተኛ የሰዓት አጠቃቀማቸውን የሚያረጋግጥ ከአመልካቹ አሰሪ ወይም ተቆጣጣሪ የሚሰጥ የፅሁፍ መሐላ
- የስራ ሃላፊነቶቻቸውን እና ዓይነተኛ የሰዓት አጠቃቀማቸውን የሚያረጋግጥ አመልካቹ በመደበኛነት አብሮ ከሚሰራው አስተማሪ፣ ረዳት አስተማሪ ወይም ሌላ ብቁ ከሆነ የኤርሊ ቻይልድሁድ ጊዜ አስተማሪ የሚሰጥ የፅሁፍ መሐላ (ቢያንስ ከአንድ ከሌላ የማስረጃ ምንጭ ጋር መጣመር አለበት)
- የስራ ሃላፊነቶቻቸውን፣ የሰሩበትን ዓይነተኛ ሰዓታት፣ እንዲሁም የሰዓት አጠቃቀም ከሚያረጋግጠው ግለሰብ የሚሰጥ የፅሁፍ መሐላ (ቢያንስ ከአንድ ከሌላ የማስረጃ ምንጭ ጋር መጣመር አለበት)
- አመልካቹ የሰሩበትን ሰዓታት እና በሁለት ሳምንታት ጊዜ ውስጥ የነበሩበትን ክፍሎች ሰንዶች የያዘ ዝርዝር የጊዜ መዝገብ (ቢያንስ ከአንድ ከሌላ የማስረጃ ምንጭ ጋር መጣመር አለበት)